የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)

SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

ግንቦት 27 ቀን 2003 ዓ. ም.

## ኢፖእአኮ በአርባ ምንጭ ተማሪዎች ላይ የሚካሄደውን አፈና ይቃወማል

በደቡብ ኢትዮጵያ፣ ጎሙጎፋ ውስጥ የአርባ ምንጭ ተማሪዎች፣ አገዛዙ ሕዳሴ እያለ ለሚጠራው ግድብ ማሠሪያ (80 ቢሊዮን ብር / 5 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ገደማ) እና አካሂደዋለሁ ለሚለው "የልማት" ሥራ ማካሄጃ የጫነባቸውን መዋጮ አንከፍልም ብለው በመቃወም እስካሁንም በአድማ ላይ ናቸው። በቢሊዮኖች የሚቆጠር ዶላር የሚያስወጣ ግድብ ለማሰራት በሚል ገንዘብ ለማሰባሰብ የተቀየሰው ይህ መዋጮ፣ በከፋ ድህነት የሚኖረውን ብዙሃኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለሀፍረት ለመዝረፍ የተቀየሰ ወጥመድ ነው።

ከጥቂት ቀናት በፊት የተጫነባቸውን መዋጮ በመቃወም ላይ የነበሩት ተማሪዎች በደቡብ ፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ በእሩምታ ተተኮሶባቸው ብዛት ያላቸው ቆስለዋል። አገዛዙ የተለመደው የከፋፍለህ ግዛው ሥልቱን አሁንም ሥራ ላይ በማዋል፣ ከአካባቢው ኗሪዎች ውስጥ የተወሰነ ብሄረሰብ አባላት የዩኒቨርስቲው ተማሪዎች ላይ ጥቃት እንዲሰነዝሩ አሰማርቷቸዋል። እነኝህ ግለሰቦችም ዱላ እና ቆንጨራ በመጠቀም፣ የዩኒቨርስቲውን አጥር ዘለው እና በሮች ሰባብረው በመግባት፣ በሰላማዊያኑ ተማሪዎች ላይ ጥቃት ፈጽመው ብዛት ያላቸውን አቁስለዋል። ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸው 7 ተማሪዎችም ሆስፒታል ገብተዋል። ከውስጣቸውም በደረሰባቸው ከፍተኛ ጉዳት ምክንያት ሕይወታቸው አስጊ ሁኔታ ላይ የሚገኝ አሉ። በአለፉት ዓመታት ታፍነው ደብዛቸው እንደጠፋው እንደ ኢዮብ፣ ደምሴና ሌሎች የኢሕአፓ አባላት፣ አሁንም የተወሰኑ ተማሪዎች ተይዘው የደረሱበት አይታወቅም።

ኢፖእአኮ አርባ ምንጭ ውስጥ በተማሪዎች ላይ የሚፈጽመውን የጭካኔ አፈና እየተቃወመ፣ መላው የዓለም ዴሞክራሲያዊ ሃይላት የመለሰ ዜናዊ አገዛዝ እያደረሰ ያለውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት አጥብቀው እንዲቃወሙ ጥሪውን ያቀርባል።

INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE

SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY
SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA
E MAIL: SOCEPP @AOL.COM
WEB SITE: WWW.SOCEPP.DE